መስከረም ፲፮ ቀን፥ ፲፱፻፺፩ ዓ.ም.

ይድረስ:-

በሥጋ ልደት ለተዛመዳችሁንና በሃይማኖት አንድነት ለተወዳጃችሁን ሁሉ፤

በያላችሁበት::

ከኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ (ንቡረ እድ) እና ከራሔል [ታደለች] ዘካርያስ::

በእግዚአብሔር ስም: ሰላምታችንን እናቀርብላችኋለን::

እኛ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት: ዕድል ፋንታችን ሆኖ: የምንኖረው: የመለኮት ቃል: በትንቢት ባመለከተን ዘመን ውስጥ መሆኑን: እስካሁን በያግጣጫው እየተከታተለ የደረሰውና እየቀጠለ የሚታየው ትንግርታዊ ሁኔታ: በሚበቃ አስገንዝቦናል:: የዚያንም ዘመን ምልክት: መለኮታዊው ቃል: እንዲህ በሚል አጠቃላይ መግለጫ አሳውቆናል:-

"በዚያን ጊዜ: ከዓለም መጀመሪያ አንሥቶ: እስከዛሬ ድረስ ያልሆነ፥ እንግዲህም ከቶ የማይሆን: ታላቅ መከራ ይሆናል፤ ...[የመምጫዬን ምልክት] ምሳሌውን: ከበለስ ተማሩ! በለስ [እስራኤል]: ጫፍዋ ማቈጥቈጥ፥ ቅጠልዋም መለምለም በሚጀምርበት ጊዜ: የመከር ወራት እንደደረሰ ታውቃላችሁ:: እንዲሁ: እናንተ ደግሞ: ይህን ሁሉ ስታዩ: [የጌታችሁ መምጫ] በደጅ እንደቀረበ እወቁ!" (ማቴ.፳፬፥ ፳፩-፴፫::)

ከዚህ የተነሣ: ቀደም ብሎ ያጥለቀለቀንን ግዙፍ የሆነውን ሥጋዊ መከራ አልፈን: አሁን ደግሞ: እጅግ ወደጸናውና ረቂቅ ወደሆነው ሃይማኖታዊ ፈተና ተሸጋግረን እንገኛለን:: ይህን መልእክት እንድንጽፍላችሁ የተገደድነውም: ፈተናው: በቀጥታ: በዚህች: በምንጋደልላት: የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን ላይ ስለመጣ ነው:: የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችንም: ቀዳማዊቷና ዘላለማዊቷ "የቅዱሱ ኪዳን ተዋህዶ ሃይማኖታችን" ናት:: ስለእርሷ የሚያብራራው ቃል: ከዚህ ጋር ተያይዞ በተላከው ዕትም ውስጥ ተጽፎ ይገኛልና: በማስተዋል ተመልከቱት::

የዚች ሃይማኖታችን ሕያው ምንነት: በቤተሰብና በቤተ ዘመድ፥ በአገር ደረጃም ሳይቀር: በትክክል እንዲታወቅ፥ እንዲጸናና እንዲጠበቅ ለማድረግ: በኢትዮጵያዊነታችን ብቻ ሳይሆን: ከወላጆቻችን ተላልፎልን በተቀበልነው ሥልጣነ ክህነት ጭምር: በተለይ በእኛ ላይ: ከልጅነት ዕድሜያችን አንሥቶ: የወረስነውን ኃላፊነትና የተረከብነውን አደራ፥ በዚህም በኩል: እስካሁን የፈጸምነውን ተግባር ሁሉ ታውቁታላችሁ ብለን እንገምታለን::

አሁን: ይህን ማሳሰቢያ የጻፍንላችሁ: ከላይ እንደጠቀስነው: የዚህኑ ተልእኳችንን ግዳጅ ለመወጣት ስንል መሆኑን ተረድታችሁ: ስለየራሳችሁና የእናንተ ስለሆኑት ደህንነት ስትሉ: መልእክቱን ለፍሬ ታበቁት ዘንድ አደራ እንላችኋለን::

ኢትዮጵያ: የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፤ መልእ.ሣ.ቁ. ፳፻፲፪፤ ስልክ ቁ. ፲፮-፲፭-፹፩፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
Ethiopia: The Kingdom of God Services, P. O. Box 43262, Washington, DC 20010, U.S.A. Tel. (301) 587-8074
Fax: 301-587-1971 E-mail: ckogycsus@aol.com Web Site: http://members.aol.com/ckogycsus

በዚህ አደራችንና ኃላፊነታችን፡ አረጋግጠን እንደተረዳነው፡ ይህ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" የሚለው፡ የዛሬው ትውልድ፡ በዚች ሃይማኖታችን ላይ፡ ማለትም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በሆነችው ባገሩ በኢትዮጵያ ላይ፡ በቤተ ሕዝቧ፥ በቤተ ክህነቷና በቤተ ምልክናዋ አማካይነት፡ ታላቅ የሆነ የክህደት፥ የዓመፅና የአመንዝራነት ኃጢአትን፡ ያለኀፍረት በይፋ ፈጽሞ ተገኝቷል። ይህን የተፈጸመውን ኃጢአት፡ ማንኛውም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ያወቀውን ያህል፡ የዓለምም ሕዝብ፡ እነሆ በገሃድ እያየው ነው። የትውልዱ ሥራ ራሱ፡ እንዲህ በግልጽ እየመሰከረ ስለሆነ፥ ይልቁንም፡ በዚህ ኃጢአት ምክንያት፡ በአድራጊዎቹ ላይ እየወረደ ያለውን የመርገም ቁጣ፡ ሁሉም የሚመለከተው ስለሆነ፡ ይህን እውነታ፡ ሊያስተባብል የሚችል ማንም የለም። ከዚህም አልፎ፡ የያንዳንዳችን ምንነትና ማንነት፡ ማለትም፡ እውነተኛነታችን ወይም ሐሰተኛነታችን፥ ታማኝነታችን ወይም ከሃዲነታችን፡ በፈጣሪያችን ፊት ብቻ ሳይሆን፡ በባዕዳኑ ሰዎችም ዘንድ ተመዝኖ፡ በይፋ መታወቁን፡ የየራሳችን ሕሊና ይመሰክርብናል።

የክህደቱ፥ የዓመፁና የአመንዝራነቱ በደል የተፈጸመባቸውንና የኢትዮጵያዊነት ተዋህዶ ሃይማኖታችን የተመሠረተችባቸውን ሰባቱን የአምላክ ኪዳናት፡ ምናልባት የማታውቁ ብትኖሩ፡ ለእናንተ ግልጽ ለማድረግ፡ ከዚህ የሚከተለውን፡ አጭር መግለጫ አቅርበንላችኋል።

፩ኛ:- በጋብቻ ሕይወታችን ምልክትነት፡ ለአዳምና ሔዋን የተሰጠችው ቃል ኪዳን፤
፪ኛ:- በሰንደቅ ዓላማችን ምልክትነት፡ ለኖኅና ልጆቹ የተሰጠችው ቃል ኪዳን፤
፫ኛ:- በኀብስትና ጽዋችን ምልክትነት፡ ለኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ የተሰጠችው ቃል ኪዳን፤
፬ኛ:- በግርዛታችን ምልክትነት፡ ለአብርሃም የተሰጠችው ቃል ኪዳን፤
፭ኛ:- በጽላትና ታቦታችን ምልክትነት፡ ለእስራኤላዊው ሙሴ የተሰጠችው ቃል ኪዳን፤
፮ኛ:- በሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ምልክትነት፡ ለዳዊት የተሰጠችው ቃል ኪዳን፤
፯ኛ:- በሥጋ ወደሙ ቁርባናችን ምልክትነት፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም የተገኘችው ቃል ኪዳን ናቸው። የእነዚህን ኪዳናት ዝርዝር ሐተታ፡ ከታች በተጠቀሱት፡ መጻሕፍትና ዕትሞች ውስጥ መመልከትና መረዳት ትችላላችሁ።

እንግዴህ፡ ይህን የመሰለው አሳዛኝ የክህደት፥ የዓመፅና የአመንዝራነት ኃጢአት እስከተከሠተበት ጊዜ ድረስ፡ እኛም፡ ከአባቶቻችንና እናቶቻችን፡ በሰውነት ልደት የወረስነውንና ገና በልጅነት ዕድሜያችን፡ በሥልጣነ ክህነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን፡ ይህን የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖት፡ ቀድሞ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በጀመርነው፥ ኋላም፡ በደርግ እሥራትና ስደት፡ ባልተቋረጠው የኢትዮጵያዊነት ተልእኳችን፡ አቅማችን በፈቀደ መጠን፡ በአገራችንና በመላው ዓለም በመዘዋወር፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" ለሚለው ወገን ሁሉ፡ ባለመሰልቸት፡ በቃልና በጽሑፍ፡ እስካሁን በግልጽ ስናሳውቅ ቆይተናል።

ዳሩ ግን፡ ይኸው ትውልድ፡ ከዚህ ሁሉ ጥረት በኋላ፡ ይልቁንም፡ የእግዚአብሔር ቅጣትና ተግሣፅ የሆነው ይህ መከራ፡ ትምህርት ሳይሆነው፡ አሁንም፡ ከሃይማኖታዊው ክህደት፥ ዓመፅና አመንዝራነት ኃጢአቱ፡ በንስሓ መመለስን እምቢ ማለቱን በኀዘን ስላረጋገጥን፡ "ኢትዮጵያዊዉና ቃል ኪዳኑ" በሚል አርእስት፡ በታኅሣሥ ፲፯ ቀን፥ ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. ታትሞ የተሠራጨ አንድ መልእክት አስተላለፍን። ያም መልእክት፡ በመደምደሚያው ላይ፡ እንዲህ የሚል፡ የውግዘት ማስታወቂያን የሚያመለክት ቃል ይዞ ይገኛል።

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፤ መልእ.ሣ.ቁ. ፵፫፻፷፪፤ ስልክ ቁ. ፲፯-፲፰-፹፩፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
Ethiopia: The Kingdom of God Services, P. O. Box 43262, Washington, DC 20010, U.S.A. Tel. (301) 587-8074
Fax: 301-587-1971 E-mail: ekogyesus@aol.com Web Site: http://members.aol.com/ekogyesus

ቃሉም:- " እንግዴህ: "ኢትዮጵያዊ ነኝ " ከሚለው: ከቤተ ሕዝቡ ሆነ ከቤተ ክህነቱ ወይም ከቤተ ምልክናው ወገን: ይህን: "የቅዱሱን ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋህዶ ሃይማኖት": በትክክል አምኖ፥ በሥርዓት ተከትሎና ሕይወቱ አድርጎ የማይኖረውን: ማናቸውንም ግለሰብ: በክህደቱ፥ በዓመፁና በአመንዝራነቱ መርገም ውስጥ እንዳለ በመቁጠር: በንስሐ ካልተመለሰ በስተቀር: በእኛ ዘንድ "ኢትዮጵያዊ" አይደለም:: በዚህ ምክንያት: ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊዉን፥ ኢትዮጵያዊነትንም በሚመለከት: በማናቸውም ነገር: እርሱ: ከእኛ ጋር፥ እኛም: ከእርሱ ጋር: ምንም ዓይነት አግባብና ግንኙነት፥ ኅብረትና አንድነት አይኖረንም::" የሚል ነው::

ይሁን እንጂ: ይህ ያለንበት ዘመን: የእግዚአብሔር የሆነው ማናቸውም ጉዳይ: እንደተራ ነገር እየታየ የተቃለለበት ጊዜ በመሆኑ: ከዘመዶቻችንና ከወዳጆቻችን መካከል: አንዳንዶች: ያን መልእክታችንን: እምብዛም አስተውለው ባለመረዳት: ወይም ለመቀበል ባለመፍቀድ: ግንኙነታችን: በሥጋዊ መልኩ ብቻ እንዲቀጥል የሚፈልጉ መኖራቸውን ስለተረዳን: ምናልባት ያሳወቁ ቢኖሩም: ለእነርሱ ጭምር: ጉዳዩን አብራርቶ ማሳወቅ ይገባል ብለን በማሰብ: ይህን ማሳሰቢያ እንደገና መጻፍና ማሠራጨት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል::

እዚህ ላይ: ከልጅነት ዕድሜያችን አንሥተን የተሸከምነውንና እስከዚህ የደረስንበትን የመስቀል ገድል ጉዞ: ለፍጻሜው ሊያበቃልን: በመለኮታዊ ሰይፍነቱ: ካፎቱ ተመዝዞ: እየቀጣና እየለየ የሚሠራውን፥ እንዲህ የሚለውን: የጌታን ቃል እንጠቅስላችኋለን:: እናንተም: የመልእክቱን ትክክለኛ ትርጉምና እውነተኛ ዓላማ: ራሳችሁ: በመንፈሳዊው አእምሮአችሁ መርምራችሁ: እንደምትደርሱበት ተስፋ እናደርጋለን::

"በሰው ፊት: በእኔ አምኖ የሚመሰክርልኝን ሁሉ: እኔም: በሰማያት ባለው: አባቴ ፊት: ስለታማኝነቱ እመሰክርለታለሁ:: በሰው ፊት የካደኝን ግን: እኔም: በሰማያት ባለው አባቴ ፊት: ክህደቱን እመሰክርበታለሁ:: ከእኔ ይልቅ: አባቱንና ወይም እናቱን የሚወድ: ለእኔ ሊሆን አይገባም፤ ሊያገለግለኝም አይችልም:: ከእኔ ይልቅ: ወንድ ልጁንና ወይም ሴት ልጁን የሚወድ: ለእኔ ሊሆን አይገባም፤ ሊያገለግለኝም አይችልም:: ለሞት የሚያበቃውን መከራ ለመቀበል ጨክኖ: መስቀሉን የማያነሣና ተሸክሞ የማይከተለኝ: ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ሊያገለግለኝም አይችልም:: ነፍሱን: በራሱ ሊያድን የሚፈልግ ሁሉ: ያጠፋታል፤ ነፍሱን: ስለእኔ የሚጥላት ግን ያገኛታል:: ወደዚህ ዓለም የመጣሁት: እንዲህ አድርጌ: ወንድ ልጅን: ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም: ከእናትዋ፥ ምራትንም: ከአማትዋ ልለይ ነው:: ስለዚህ ሰው: እኔን እንዳይከተልና እንዳያገለግለኝ: ቤተሰቦቹ ሳይቀሩ ጠላቶች ይሆኑበታል:: በምድር ላይ: ሰይፍን እንጂ: ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ! " ያለውም ስለዚህ መሆኑን መረዳት ይገባል:: ( ማቴ. ፲፥ ፴፪-፴፱ )

የመለኮት ሰይፍ ሆኖ: እውነተኛውን: ከሐሰተኛው፥ ታማኙን: ከከሃዲው፥ የእግዚአብሔር የሆነውን: የዲያብሎስ ከሆነው: ፈጽሞ ሊለይ በታወጀው: በዚህ ቃል መሠረት:-

እኔ ኂሩተ ወልድ (ኤርምያስ): ከአባቴ ከተክለ ሥላሴ (መምሬ ከበደ ወልደ ኢየሱስ) እና ከእናቴ ከወለተ ሚካኤል (እማሆይ አባይነሽ ዮሴፍ)፥

እኔም ኂሩተ ማርያም (ራሔል [ታደለች]): ከአያቴ ከንዋየ ክርስቶስ (አለቃ ዘካርያስና) ከእናቴ ከእህተ ማርያም (እማሆይ ድንስር ገብረ እግዚአብሔር): ሁለታችንም: በቃል ኪዳን ወርሰንና በሥልጣነ ክህነት አጽንተን: እያገለገልን የምንኖርባት፥ ለልጆቻችን የምናወርሳትና ለእናንተም አሳውቀን የምናስረክባት: የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን: ከዚህ ጋር በተያያዘው ዕትም ውስጥ ተገልጻ የተጻፈችው ናት::

ኢትዮጵያ: የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፣ መልእ.ሣ.ቁ. ፵፫፻፷፪፣ ስልክ ቁ. ፲፯-፲፰-፹፩፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Ethiopia: The Kingdom of God Services, P. O. Box 43262, Washington, DC 20010, U.S.A. Tel. (301) 587-8074
Fax: 301-587-1971 E-mail: ekogyesus@aol.com Web Site: http://members.aol.com/ekogyesus

ስለዚህ፡-

፩ኛ:- በሃይማኖት፡ ፍጹምነት እንጂ፡ አላዋቂነትና ማድበስበስ፥ ጥርጥርና ውልውል፥ ልልነትና ግዴለሽነት ሊኖር ስለማይገባ፡ እናንተም እኛም፡ በቀጥታ ከእግዚአብሔር፡ በቃል ኪዳን የተቀበልናትን፥ በአባቶቻችንና እናቶቻችንም አማካይነት የወረስናትን፥ በሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናትም የጸናችውን፡ ይህችን፡ የጠራችና የቀናች፥ የተገለጠችና የታወቀች፥ እውነተኛዋንና ቀዳማዊቷን ሃይማኖታችንን፡ በትክክል ተረድታችሁና ሕይወት አድርጋችሁ፡ ልትኖሩዋት ይገባችኋል።

፪ኛ:- ባሁኑ ዘመን፡ ዲያብሎስ፡ በራሳችን ወገኖችና በባዕዳን ጠላቶች መሣሪያነት፡ ይህችን ሃይማኖት ለማጥፋት፡ በረቂቅና በግዙፍ ኃይል የሚያካሂደውን ዘመቻ በዓይናችሁ የምታዩት ነውና፡ ይህንኑ ተገንዝባችሁ፡ እስከመሥዋዕትነት በሚደርስ ፍቅር፡ በየግላችሁም ሆነ በኅብረት፡ ነቅታችሁና ተግታችሁ ልትጠብቋት፥ ለልጆቻችሁም ልታስተላልፏት ይገባችኋል።

፫ኛ:- ስለዚች ሃይማኖታችሁ በበለጠ ለማወቅና ለመረዳት የምትፈልጉት ካለ፡ በዚህ ጽሑፍ፡ በየገጹ ግርጌ በተመለከቱት አድራሻዎቻችን፡ ልትጠይቁን፥ በግንባርና በስልክም ልታነጋግሩን የሚቻል ከመሆኑ ጋር፡ "የኢትዮጵያ ጥሪ ለልጆቿ" እና "Ethiopia: The Classic Case" በሚል አርእስት የወጡትን መጻሕፍቶቻችንን፥ ሌሎችንም የወደፊት ዕትሞቻችንን መመልከቱ ስለሚጠቅማችሁ፡ እነዚህን በማንበብ፡ የኢትዮጵያዊነታችሁንና የሃይማኖታችሁን እውቀት ልታሰፉና ልታጠናክሩ ይገባችኋል።

እንግዴህ፡ በእናንተና በእኛ መካከል ላለው ዝምድናና ወይም ወዳጅነት፡ ዋናው ማገናኛ ድልድይ፡ ይህ፡ የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን መሆኑ፡ በእኛ ዘንድ የሚታወቀውን ያህል፡ በእናንተም በኩል ይታወቃል ብለን እናምናለን። ይኸው ዝምድናችንና ወይም ወዳጅነታችን፡ እስካሁን ጸንቶ የቆየው፡ ሁላችንም፡ ይህንኑ ሃይማኖታችንን፡ በያለንበት ጠብቀን በመገኘታችን መሆኑ እርግጥ ነው። ለወደፊትም በመልካም ሊቀጥል የሚችለው፡ ከዚሁ ሃይማኖታችን እስካልተነዋወጥን ድረስ መሆኑ፡ ሊታወቅ ይገባል። ይህም ማለት፡ በዚህ ሃይማኖታችን ከተለያየን፡ በመካከላችን፡ ምንም ዓይነት ዝምድና ወይም ወዳጅነት አይኖርም ማለት ነው።

ስለዚህ፡ ዝምድናችንና ወዳጅነታችን፡ በእግዚአብሔር ፊት እውነተኛ ሆኖ፡ በጤናማነት ይቀጥል ዘንድ፡ ጥንታዊት የሆነች፡ ይህችን ሃይማኖታችንን፡ እኛ፡ በዚህ ጽሑፍ፡ ገልጸን እንዳቀረብንላችሁ፡ ሕይወታችን አድርገናት እንደምንኖራት ሁሉ፡ እናንተም፡ ሕይወታችሁ አድርጋችኋት በመኖር፡ ለየራሳችሁና ለእግዚአብሔር፥ ለሰውም ሁሉ፡ በምግባራችሁ አረጋግጣችሁ፡ የምትገልጧት እንደምትሆን እንተማመናለን።

በመጨረሻ፡ ይህ መልእክታችን የደረሳችሁ መሆኑንና በቃል ወይም በጽሑፍ፡ የምትሰጡን መልስ ቢኖር፡ ይህንኑ እንድታስታውቁን የምንጠብቅ መሆናችንን፥ ምናልባትም፡ ይህ መልእክት ሊደርሳቸው ይገባል የምትሏቸው ዘመዶችና ወዳጆች ቢኖሩ፡ ይህንኑ ብታስተላልፉልን፡ አምላካዊዉን በረከት የምታገኙበት መሆኑን በአክብሮት እንገልጽላችኋለን።

አገራችንን ኢትዮጵያን፡ ከእኛ ልጆቿ ጋር የሚመሩዋትና የሚጠብቋት፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም፡ ሁላችንንም፡ በኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ እስከመጨረሻው የጸናን ሆነን ለመገኘት ያበቁን ዘንድ በያለንበት እንጸልያለን።

ራሔል ዘካርያስ

ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ
( ንቡረ እድ )

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት፤ መልእ.ሣ.ቁ. ፰፻፲፱፤ ስልክ ቁ. ፲፩-፲፰-፹፭፤ አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
Ethiopia: The Kingdom of God Services, P. O. Box 43262, Washington, DC 20010, U.S.A. Tel. (301) 587-8074
Fax: 301-587-1971 E-mail: ekogyesus@aol.com Web Site: http://members.aol.com/ekogyesus